# *I. ወቅታዊ ሁኔታዎችና የመንግስት አቋሞች*

ይህ አጭር ማስታወሻ ወቅታዊ ጉዳዮችንና በነዚህ ላይ መንግስት ያለውን አቋም ለማሳወቅ እንዲሁም ከማንኛውም ሶስተኛ ወገን ጋር በሚደረግ ግንኙነት የመንግስትን አቋም በትክክል ለመግለፅ ይቻል ዘንድ በመንግስት የኮምዩኒኬሽን ጉዳዮች ፅህፈት ቤት ተዘጋጅቶ የቀረበ ነው። በአሁኑ ጊዜ ጐላ ብለው የሚታዩት የፖለቲካ ጉዳዮች ከሰ ራዊታችን ሶማሊያን ለቆ መውጣት፣ ከበጐ አድራጐት ድርጅቶች ህግ መፅደቅና የአንድነት ለፍትህና ዴሞክራሲ ርቲ ሊቀመንበር መታሰር ጋር የተያያዙ ናቸው። ፅ/ቤቱ ወደፊትም ጐል ተው በሚወጡ ጉዳዮች ላይ የመንግስትን አቋሞች በተመሳሳይ መንገድ የሚያሳውቅ ሲሆን በሶስቱ ጉዳዮች ላይ ያለው ሁኔታና የመንግስት አቋም ከዚህ የሚከተለው ነው።

## 1. ሰራዊታችን ከሶማሊያ ለቆ መውጣቱን በተመለከተ፣

### የሶማሊያ ተልእኳችን በተሳካ ሁኔታ ተፈፅሞ ሰራዊታችን ወደአገሩ በመመለስ ላይ ስለመሆኑ፣

ወደሶማሊያ ለመግባት የተገደድነው በኤርትራ መንግስት አቀናባሪነትና መሪነት በሶማሊያ አክራሪ ሃይሎችና በአገር ውስጥ ባሉ ተባባሪዎቻቸው ተጨባጭና ወቅታዊ አደጋ በአገራችን ላይ በመደቀኑ ነበር። የሶማሊያ ጣልቃ ገብነታችን ዋነኛ አላማ ይህን በሶስት ሀይሎች የተቀናጀ አደጋ ለማስወገድና ለልማትና ዴሞክራሲያዊ ጉዟችን መፋጠን ብሎም ለአገራችን ደህንነት አስተማማኝ ከባቢያዊ ሰላም መፍጠር ነበር። ይህን መሰረታዊ ተልእኮ በአገራችን ላይ ወረራ ለማካሄድ ያላቸውን ውጥን በተደጋጋሚ በማወጅ የገለፁትን አክራሪ ሃይሎች ከሁለት ሳምንት ባልበለጠ ጊዜ በመሰባበር ለማስወገድ ችለናል። ይህ የሶማሊያ ተልእኳችን ወሳኝ ድላችን ነው።

ይህን ተልእኮ በተሳካ ሁኔታ ከፈፀምን በኋላ በአገሪቱ ለሰላም መስፈን የተፈጠረውን እድል በመጠቀም ሰላም እንዲሰፍን ላለፉት ሁለት አመታት በሶማሊያ ውስጥ ሰላምና መረጋጋት ለማስፈን ጥረት ስናደርግ ቆይተናል። በዚህ ጥረት የምንፈልገውን ያህል ሰላማዊ ሁኔታ ፈጥረን ሶማሊያ ወደተረጋጋ መንግስታዊ ስርአት

እንድትሸጋገር ለማድረግ ባንችልም ለሶማሊያ ሰላም የበኩላችንን ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክተናል፡፡

በአሁኑ ጊዜ በሽግግር መንግስቱና በARS መካከል ጅቡቲ ለይ ኢትዮጵያ እስከ ታህሳስ መጨረሻ ሶማሊያን ለቃ እንድትወጣ በተደረሰበት ስምምነት መሰረት ሰ ራዊታችን ሶማሊያን ለቆ በመውጣት ላይ ይገኛል፡፡ ከሶማሊያ ለቀን የመውጣታችን ሂደት በተሳካ አኳኋንና የጐላ ችግር ሳይገጥመው እየተከናወነ ይገኛል፡፡ ይሁንና ከመውጣታችን ጋር ተያይዞ በውስጥም በውጭም ያሉ አፍራሽ ሃይሎች በሶማሊያ ያለን ቆይታ ስኬታማ እንዳልነበር ለማስመሰል እየተጣጣሩ ይገኛሉ፡፡ እነዚህን መነሻ በማድረግ በዚህ ጉዳይ ዙሪያ ያሉት የመንግስት አቋሞችና መልእክቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- በሶማሊያ ውስጥ ያደረግነው ጣልቃ ገብነትና ይህንኑ ተከትሎ ለሁለት አመታት በቆየንበት ጊዜ ሁሉ የኢትዮጵያን ደህንነትና ብሄራዊ ጥቅም ያስጠበቁ ድሎች ተጐናፅፈናል፡፡
- የመጀመሪያውና ወሳኙ ድል በሻእቢያ መንግስት አቀናባሪነት፣ በሶማሊያ አክ ራሪዎች ግንባር ቀደምትነትና በውስጥ አፍራሽ ሃይሎች ተባባሪነት ከሶስት አቅጣጫ በአገራችን ላይ ተደቅኖ የነበረውን ወቅታዊና ተጨባጭ አደጋ በተሳካ ሁኔታ ለማምከን መቻላችን ነው፡፡ ይህ ድል ሰራዊታችን በእስላማዊ ፍርድቤቶች ውስጥ የነበሩትን አክራሪ ሃይሎችና ወታደራዊ አቅማቸውን በመስበር ከሁለት ሳምንታት ባልበለጠ ጊዜ የተጐናፀፍነው የመጀመሪያው ታላቅ ድል ነበር፡፡
- በአክራሪዎች ላይ የተጐናፀፍነውን ድል ተከትሎ በሌሎች ግንባሮች ተሰልፈው የነበሩት የጥፋት ሃይሎች በተለይም የኤርትራ መንግስት ያሰበው ካለመሳካቱም በላይ ይበልጥ በኢኮኖሚ እየተዳከመና በፖለቲካም ውስጣዊ ቀውስ ውስጥ ተዘፍቆ የሚገኝበት ሁኔታ እየተባባሰ እንዲሄድ ለማድረግ ችለናል፡፡
- ባለፉት ሁለት አመታት በሶማሊያ ቆይታችን አቅማችን የፈቀደውን ያህል በአገሪቱ ሰላም ለማስፈን፣ በጐሳዎች መካከል ተፈጥሮ የቆየውን ግጭትና መቃቃር ለመፍታትና እርቀሰላም ለማውረድ ጥረት አድርገናል፡፡ የአልሸባብን ወታደራዊ አቅም ለመስበር በወሰድናቸው ተደጋጋሚ እርምጃዎች አልሸባብ በአሁኑ ጊዜ ወደተራ የአሸባሪ ድርጅትነት እንዲወርድም አድርገናል፡፡
- የኢትዮጵያ ሰራዊት ከሶማሊያ ለቆ እየወጣ ያለው በተረጋጋና ተልእኮውን በተሳካ ሁኔታ በፈፀመበት ወቅትና ሁኔታ መሆኑ፣ ሰራዊቱ በሶማሊያ ቆይታው

የኢትዮጵያ ህዝቦችና በአገራችን በመገንባት ያለው ህዝባዊ ስርአት እውነተኛ ተወካይ መሆኑን በተግባር አረጋግጧል፡፡

- በሶማሊያ ዘላቂ ሰላም ለማምጣት ኢትዮጵያ፣ የሶማሊያ ሰላም ወዳድ ሃይሎችና የኢጋድ አባል አገራት እንዲሁም የአፍሪካ ህብረት በመተባበር ያደረጉት ርብርብ ተስፋ ሰጭ የሰላም እድል ከፍቶ የነበረ መሆኑ፣ ይሁን እንጅ ከችግሩ የሚመጥን መፍትሄ የማቅረብ ጉዳይ የተባበሩት መንግስታት ድርጅትና የአለም አቀፍ ማህበረሰብን የላቀ ትብብር የሚጠይቅ ጉዳይ የነበረ በመሆኑና በዚህ ረገድ የነበረው ድጋፍ አናሳ መሆኑ፣
- ይህ ውሱንነት እንዳለም ሆኖ ኢትዮጵያ በሶማሊያ ጉዳይ ላይ ገንቢ ሚና ለመጫወት አቅሟ የፈቀደውን ሁሉ ማድረጓና ሰራዊታችንም አገራዊና አፍሪካዊ ግዳጁን በተሳካ ሁኔታ የፈፀመ መሆኑ፣
- ኢትዮጵያ ከአሁን በኋላም በአንድ በኩል ለሶማሊያ ሰላምና መረጋጋት አቅሟ የፈቀደውን አስተዋፅኦ ለማበርከት ወደኋላ የማትልበት ሁኔታ ያለ መሆኑ፣ በሌላ በኩል ሶማሊያን ለቀን ከመውጣታችን ጋር ተያይዞ ከሶማሊያ አክራሪዎች በኩል ሊቆጣ የሚችል አሸባሪ ተግባር ካለ ይህን ለመመከት ብቃቱ ያለን መሆኑ፣

## 2. የበጐ አድራጐት ድርጅቶች ህግን በተመለከተ፣

በአገራችን የበጐ አድራጐት ድርጅቶችን በተመለከተ ህግ ከመውጣቱ በፊት ሰፊ የማጥላላት ዘመቻ ሲካሄድብን ቆይቷል፡፡ ይህ ዘመቻ ህጉ ከወጣ በኋላም ቢሆን አልተቋረጠም፡፡ በመሆኑም በጉዳዩ ላይ መንግስት ያለውን አቋም ደግሞ ደጋግሞ ማስረዳት አስፈላጊ ሆኖ ይገኛል፡፡ ዘመቻው በዋነኛነት የአገራችንን ሉአላዊ ህግ የማውጣት መብት ባለመቀበል መያዶችን የተልእኳቸው ማስፈፀሚያ አድርገው ከሚመለከቱ የውጭ ሃይሎችና በአገር ውስጥ ደግሞ በዋነኛነት የውጭ ሃይሎችን ገንዘብና ርዳታ በመጠቀም በውስጥ የፖለቲካ ጉዳያችን ላይ ወሳኝ ሚና መጫወት ከሚፈልጉ ሃይሎች በመመንጨት እየተካሄደ ያለ ነው፡፡ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች የገንዘብ ድጋፍም ሆነ የኑሮ ደረጃ መሻሻል ለውጥ የማይጠብቀው አብዛኛው የአገራችን ህዝብ በጉዳዩ ላይ የመንግስትን አቋም የሚነቅፍበት ሁኔታ የለም፡፡ ይልቁንም ለመንግስት የቁጥጥር አቋም ድጋፍ አለው፡፡ ነገር ግን ይህም ሆኖ በጉዳዩ ላይ የተሟላ ግልፅነት የሌለ በመሆኑ ድጋፉ የሚፈለገውን ያህል ጠንካራ ነው

ማለት አይቻልም። ስለዚህም በዚህ ጉዳይ ላይ የህዝቡን ግልፅነት የተሟላ ለማድረግ ሲባል ለሚከተሉት ጉዳዮች ልዩ ትኩረት በመስጠት ማብራራት ያስፈልጋል።

- መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በተመለከተ መንግስት ያለው አቋም ድርጅቶቹን በሁለት ክፍሎ የሚመለከት እንደሆነ፣ በአንድ በኩል በዜጎች ፍላጎት፣ ጥረትና የገንዘብ አቅም የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች እንዳሉና እነዚህ በህገመንግስታችን የተከበረና መንግስት ሊሰጣቸውም ሊከለክላቸውም የማይችል የዜግነት መብት ያላቸው እንደሆኑ፣
- በሌላ በኩል አብዛኛውን ገቢያቸውን ከውጭ በሚገኝ ገንዘብ ላይ በመመስረት ፕሮጀክት ቀርፀው የውጭ ሃይሎችን ፍላጎት (ቀናም ይሁን የተሳሳተ) ለማሳካት የሚንቀሳቀሱ መያዶች ያሉ መሆናቸው፣ መንግስት እነዚህን የዜግነት መብትን ለማስጠበቅ የተፈጠሩ አደረጃጀቶች አድርጎ የማይመለከታቸው መሆኑ፣
- ዜጎች ለመብታቸው ለመሟገት የውጭ ገንዘብ የማያስፈልጋቸው ከመሆኑም በላይ የውጭ ገንዘብ ሳያገኙ ለዘመናት ለመብታቸው በተለያዩ አደረጃጀቶች ታቅፈው ሲደራጁ የኖሩ መሆናቸው፣
- አዲሱ ህግ በውጭ ገንዘብ የሚንቀሳቀሱ የውስጥና የውጭ ድርጅቶች በማህበ ራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት መስኮች እንዲሳተፉ የሚያደርግ መሆኑ እንደተጠበቀ በፖለቲካ ጉዳይ ላይ ግን ተሳትፎ ሊያደርጉ እንደማይችሉ ገደብ ማስቀመጡ ሉአላዊነታችንን የሚያስጠብቅና ፈፅሞ ለድርድር የማይቀርብ ጉዳይ እንደሆነ፣
- አንዳንድ የውጭ ሃይሎች ይህ ህግ እንዳይወጣ ግፊት ሲያደርጉ የነበሩ ከመሆን አልፈው ህጉ በመውጣቱ የዜጎች የፖለቲካዊ ተሳትፎ መድረክ ጠቧል በማለት እርዳታ እናቋርጣለን እስከማለት የሚደርሱ መሆናቸው፣
- እርዳታው መቋረጥ አለመቋረጡ ወደፊት የሚታይ ሆኖ ኢትዮጵያ የራሷን ጥቅምና ሉአላዊነት ለማስከበር የሚያስችል ህግ ማውጣት የለባትም የሚለው አስተሳሰብ በይዘቱ የቅኝ ገዥነት ባህሪ የተጠናወተው በመሆኑ ፈፅሞ ተቀባይነት የሌለው መሆኑ፣
- መንግስት ህጉን በተግባር ላይ ለማዋል በሚያደርገው እንቅስቃሴ በልማት ስራ ላይ የሚሰሩትን ለማገዝና ከነሱ ጋር ለመተባበር አቅሙ የፈቀደውን ሁሉ ከማድረግ ሳይቆጠብ በወሳኝነት በውጭ ገንዘብ የሚንቀሳቀሱ መያዶች በውስጥ

ፖለቲካዊ ጉዳያችን ላይ አንዳችም ጣልቃገብነት እንዳይኖራቸው የሚያደርግ መሆኑ፣

- ዜጐች ለመብቶቻቸው መከበር የሚመሰርቷቸውን ራስ አገዝ ድርጅቶች ለማጠናከርና ከነሱም ጋር በፖለቲካ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ ጉዳዮች ወዘተ ሁሉ ተመካክሮ ለመስራት ልዩ ትኩረት የሚያደርግ መሆኑ በዚህ ጉዳይ ላይ ያሉን አቋሞች ናቸው::

## 3. በአንድነት ለፍትህና ዴሞክራሲ ርቲ ሊቀመንበር መታሰር ላይ የመንግስት አቋም፣

የአንድነት ለፍትህና ዴሞክራሲ ርቲ ሊቀመንበር ህገመንግስታዊ ስርአቱን በሃይል ለመገልበጥ ባደረጉት ተሳትፎ ምክንያት ተከሰው ከተፈረደባቸው በኋላ ባቀረቡት የይቅርታ ጥያቄ መሰረት መንግስት ጉዳዩን ተመልክቶት ቅድመ ሁኔታ ያለው ይቅርታ (Conditional pardon) እንዲሰጣቸው በመወሰኑ በ1999 ዓ/ም ማብቂያ ላይ ከእስር ተለቀዋል:: ይሁንና ሊቀመንበሯ በተለያዩ አጋጣሚዎች ይቅርታ እንዳልጠየቁ በማስመሰል ለደጋፊዎቻቸውና ለመላው ህዝብ ተደጋጋሚ መግለጫዎች መስጠታቸውን ተከትሎ መንግስት በጉዳዩ ላይ ያላቸውን አቋም እንዲያብራሩ ጠይቋቸዋል:: በዚህም ጊዜ ሊቀመንበሯ ይቅርታ የጠየቁበት ሁኔታና አጋጣሚ እንደሌለ ገልፀዋል:: ከዚህ በመነሳት በመንግስት በኩል ይቅርታ አልጠየቅኩም እስካሉ ድረስ አቋማቸው ከዚህ ቀደም የጠየቁትን ይቅርታ በመናድ ላይ የተመሰረተ ከመሆኑም በላይ ይቅርታውን የሚያፀናላቸው አንዳችም የመፀፀት መንፈስ እንዳላሳዩ የሚያሳይ በመሆኑ ህጉን ተከትሎ የሰጣቸውን በ ቅድመ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ይቅርታው አንስቶታል:: ሊቀመንበሯም በፍርድ ቤት የተሰጣቸውን የእስር ብይን እንዲፈፅሙ በማድረግ የህግ የበላይነት ያለልዩነት ተግባራዊ እንዲሆን አድርጓል::

ከሊቀመንበሯ እስራት ጋር ተያይዞ በአገር ውስጥና በውጭ የሚገኙ ደጋፊዎቻቸውና በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባት የሚፈልጉ ሃይሎች ሁሉ ሰፊ ዘመቻ በማካሄድ ላይ ይገኛሉ:: ዘመቻው የሚገለፅባቸው የተለያዩ መልኮች ያሉ ቢሆንም ከይዘት አኳያ ዋነኞቹ የህግ የበላይነት መከበር የለበትም፣ ግለሰቧ ህግ ቢጥሱም መንግስት አይቶ እንዳላየ ማለፍ አለበት፣ እንዲሁም መንግስት ጥያቄያችንን ተቀብሎ ሊቀመንበሯን ካልለቀቃቸው በሰላማዊ ሰልፍና በልዩ ልዩ ዘመቻዎች እንዲሁም እርዳታ

እንደሚቋረጥ በማስፈራራት ፋታ እንዲያጣ እናደርገዋለን የሚሉ ናቸው:: በነዚህ ጉዳዮች ላይ የመንግስት አቋም:-

- የአንድነት ለፍትህና ዴሞክራሲ ፓርቲ ሊቀመንበር የጠየቁትን ይቅርታ እንዳልጠየቁና የተፈቱት የአገር ውስጥና የውጭ ደጋፊዎቻቸው መንግስትን በትግል አስገድደው በማንበርከካቸው እንደሆነ በማስመሰል በተደጋጋሚ የሰጡት መግለጫ ስህተት መሆኑ፣ ከእስር የተለቀቁት ይቅርታ በመጠየቃቸውና መንግስትም በቅድመ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ይቅርታ ስለሰጣቸው ብቻ መሆኑ፣
- ሊቀመንበሯ ይህን እውነታ ክደውና ለፈፀሙት ወንጀል አንዳችም የመፀፀት መንፈስ ሳያሳዩ ይቅርታ አልጠየኩም እስካሉ ድረስ ያልጠየቁት ይቅርታ ሊሰጣቸው የማይገባ በመሆኑ የፍርድ ውሳኔውን እንዲፈፅሙ ማድረግ የህግ የበላይነትን የማስከበር ጉዳይ መሆኑ፣
- መንግስት የህግ የላይነትን የማስከበር ሃላፊነቱን መወጣቱ በአገራችን ለሰላምና መረጋጋት፣ ለእድገትና ለዴሞክራሲ ዋስትና በመሆኑ በዚህ ጉዳይ ላይ ፈፅሞ ለድርድር የሚቀርብ አቋም የሌለውና ሊኖረውም የማይገባ መሆኑ፣
- የሊቀመንበሯ ድርጅት አባላትና አመራሮችም ሆነ ሌሎች ደጋፊዎች፣ እንዲሁም የመንግስትን እጅ በረባ ባልረባው መጠምዘዝ የሚፈልጉ የውጭ ሃይሎች በዚህ ጉዳይ ላይ የሚያካሂዱት ዘመቻም ሆነ ግፊት ፈፅሞ የማይሰራ እንደሆነና መንግስት ህግን የማስከበር ሉአላዊ ሃላፊነቱን ለማንም አሳልፎ ለመስጠት ዝግጁ አለመሆኑ፣
- መንግስት ግለሰቧን ለማሰር/ላለመፍታት የወሰነው የህግ የበላይነትን የማስከበር ግዴታውን ከመወጣት ሃላፊነቱ በተጨማሪ የአገራችን ህግ ለሁሉም ዜጐች እኩል የሚያስተናግድ እንጅ ሰላማዊ ሰልፍና በጩኸት ላይ የተመሰረተ ተቃውሞ የሚያሰማ ወገን ላለው ፖለቲከኛና ታዋቂ ግለሰብ አንድ ህግ፣ የድጋፍ ሰልፈኛ ለሌላው ዜጋና ምስኪን ሌላ ህግ ማውጣትም ሆነ ተግባራዊ ማድረግ ፈፅሞ ተቀባይነት የሌለው መሆኑ፣

- ከግለሰቧ መታሰር ጋር ተያይዞም የፖለቲካ መድረከ ይጠባል የሚለው ስጋትና ወቀሳ መሰረተ ቢስ መሆኑ፣ መንግስት ዜጐች በህገ መንግስቱ የተጐናፀፉት መብት ምንጊዜም እየሰፋ በሚሄድ አኳኋን ተግባራዊ የሚደረግ መሆኑ እንደተጠበቀ ከህገ መንግስታዊ ስርአቱ ውጭና ይህንኑ በሚንድ መልኩ የፖለቲካ መድረክን የማስፋት ጉዳይ ፈፅሞ የማይታሰብና ለድርድር የማይቀርብ ጉዳይ ነው የሚል የፀና አቋም አለው፡፡